# ጠላትን ፈጥሮ መዋጋት

## (በቼችንያ ህዝብ ላይ የተፈጸመው ደባ ምስጥር)

በ1990 መጀመሪያ የሶቭየት ህብረትን መፍረክረክ ተከትሎ በህብረቱ አባል ሃገራት ህዝቦች ዘንድ ለረዥም አመታት ተዳፍኖ የነበረው በማንነት ላይ የተመሰረተ ብሄራዊ መንግስትን (nation state) የመፍጠር እንቅስቃሴ በማንሰራራቱ ሶቭየት ህብረት በ1991 ፈርሳ በምትኳ 15 ሉኡላዊ አገሮች መፈጠር ቻሉ ።

በተመሳሳይ ሁኔታ በዚህ ወቅት በቼችኒያም በእስታሊን አረመናዊ የዘር ማጥፋት እርምጃ ተዳፍኖ የነበረው በማንነት ላይ የተመሰረተን ብሄራዊ መንግስት (nation state) የመፍጠር እንቅስቃሴ ከተዳፈነበት መቀስቀስ ችሏል። ይህም በአዲስ መንፈስ የተነሳሳው የነጻነት እንቅስቃሴ ግርማ ሞገስ ያለው (chrasmathic) መሪ በማፈላለግ ላይ እያለ ከክልሉ ቢርቅም የማህበረሰቡን ጉዳይ ይከታተል የነበረ በ1990 ዎቹ መጀመሪያ በቸችኒያ ፖለቲካ ትልቅ ሚና የተጫወተው የቸቺኒያው ተወላጅ ጁሃር ዱዳየቭ ወደ ቸችኒያ ግዛት ተመለሰ ።

የዱዳየቭ ቤተሰቦች እንደ አብዛኛዎቹ ቼችንያዊያን የእስታሊን የግዞት ሰለባ ስለነበሩ ከእስታሊን ህልፈት በኃላ ወደአገራቸው ከተመለሱ ሊጋ ወጣቶች መካከል አንዱ ነበር ። በቤተሰቦቹና በወገኖቹ ላይ ተፈጽሞ የነበረው ግፍ በአሥራዎቹ ዕድሜ ላይ ጥልቅ የሆነ ተጽዕኖ እንዳሳደረበት ይታመናል። ዱዳየቭ ብሩህ ከሚባሉት ወጣቶች አንድ ቢሆንም በሶቪየት ሥርዓት ውስጥ ለቼቼንያ ተወላጆች ቁልፍ የሆኑ ፖለቲካዊ ፣ ወታደራዊ ሆነ አስተዳደራዊ ሥልጣን ክልክል ስለነበር ዱዳየቭ ራሱን እንደ ሌላ ብሄረሰብ (Ossetian) ተወላጅ አድርጎ በማቅረብ ከሶቪየት ሥርዓት ለመቀላቀል ተገዶ ነበር። በዚህ መንገድ የከፍተኛ ትምህርቱን ካገባደደ በኃላ በሰራዊት አባልነት በማገልገል የተፋጠነ እድገት ለማግኘት በመቻሉ በአጭር ግዜ ውስጥ ለኮሎኔልነት ማዕረግ መብቃት ችሏል ። በመቀጠልም በሶቪየት አየር ኃይል የፓይለትነት ስልጠና ካጠናቀቀ በኃላ በአፍጋኒስታን ጦርነት ወቅት ሃገሩን ሶቪየት ህብረትን አገልግሏል። በመጨረሻም በኢስቶኒያ (በታርቱ) የ23 ኛው ስትራቴጂክ ቦንብ ጣይ ክፍል አዛዥነት ማእረግ አገኘ። በዚህም ወቅት በ1917 ፊንላንድ ከሩሲይ የበላይ ተቆጣጣሪነት የተላቀቀችበትን ዲሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ በማጥናት እና በ1990 በእስቶኒያ ፣ በላትቪያ እና ሉትዌኒያ ከሶቪየት ሥርዓት ለመላቀቅ የተጀመረዉን ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ በቅርበት በመከታተል ላይ ትኩረት ጥሎ እንደነበር ይነገራል። ይህ በእንዲህ እንዳለ ከወቅቱ የሶቪየት አመራር በኢስቶኒያ ፣ በላትቪያ እና ልትዌኒያ የተነሳዉን ህዝባዊ እንቅስቃሴ ለማዳፈን እሱ የሚያዘው ሃይል እርምጃ እንዲወስድ ሲታዘዝ ትዛዙን ዉድቅ በማድረጉ ከስራው ስለተሰናበተ ወደ ቼቺኒያ አቀና ።

ዱዳየቭ ወደ ቼችንያ የተመለሰበት ወቅት የሶቭየት ህብረት ሃይል በመፍረክረክ ላይ የነበረበትና Perestroyka (ግልጽነት) በመባል የሚጠራው የጎርቫቾቭ መንግስት የለውጥ መርሆ በስራ መተርጎም የጀመረበት ግዜ ስለነበር የተፈጠረውን እድል በመጠቀም በማቆጥቆጥ ላይ የነበረውን በቼችኒያ ብሄራዊ መንግስት (nation state) የመፍጠር እንቅስቃሴ በፍጥነት ለመቀላቀል ቻለ። በእስቶኒያ ፣ በላትቪያ እና ሉትዌኒያ የተነሳዉን ለነጻነት የሚደረግ ትግል ደግፎ የሶቪየትን አመራር ትእዛዝ ውድቅ በማድረግ ባገኘው ታዋቂነት በመታገዝ በአጭር ግዜ ዉስጥ የቼቼኒያ ብሔራዊ ኮንግረስ መሪ ሆኖ ተመረጠ። ከዚያም በ27 October 1991 በሶስት ተፎካካሪዎች መካከል የተደረገውን አገራዊ ምርጫ አሸንፎ የቼቼንያ የመጀመሪያው ፕረዝደንት ለመሆን በቃ። ከአንድ ወር በኋላ በ November 1991 ቼቼኒያ ነጻነቷን አወጀች ። በዱዳየቭ የሚመራው መንግስትም እቅዱ በኢስቶኒያ ፣ በላትቪያ፣ ሉትዌኒያ እና ሌሎቹም ከሶቮት የተገነጠሉ አገሮች ለመገንባት የሚጥሩትን ሴኩላር እና ዲሞክራሲያዊ ስርአት መገንባት መሆኑን ባወጣው ህገ-መንግስት በግልጽ አሳወቀ።

ሊጋው የቼቺኒያ መንግስት ከ1991-1994 አገሪቱን በተቀላጠፈ መንገድ በመገንባት አገር የማስተዳደር ችሎታዉን ከማሳየቱም በላይ ከ 1994-1996 የመጀመሪያዉ የቸችንያ ጦርነት ተብሎ የሚጠራዉን በአገሪቱ ላይ በራሺያ ሃይሎች የተደረገዉን ወረራ በማምከን አገሪቱን ለመከላከል ብቃት ያለው መሆኑን አረጋገጠ። በ 1997 በተደረገው ምርጫ የቼቼንያ ህዝብ በቼቼንያ እስላማዊ መንግስት

ለመስረት አቅድ እንደ ነበረው ከሚነገርለት ሻሚል ባሳየቭ ይልቅ በሴኩላር እይታው ታዋቂ የነበረዉን Aslan Maskhadov ን በ 66% ድምጽ መምረጡና አሸፊዉም አስላን በሰላማዊ የስልጣን ሽግግር የፕሬዝደንትነቱን ስልጣን መረከቡ ቼችንያ ሰኩላር በሆነ ዲሞክራሲያዊ ጎዳና ለመጓዝ የቆረጠች መሆኗን አስመሰከረች ፡፡

የቼችንያ የፖለትካ ልሂቃን መርህና መግለጫዎች ከሌሎች ሴኩላር የምስራቅ አውሮፓ የፖለቲካ ልሂቃን ጋር ተመሳሳይ መሆንና ድርጊታቸዉም ሴኩላርና ዲሞክራሳዊ መሆናቸዉን ይፋ ማድረጉ የሩሲያ መንግስት የቼችንያን መንግስት በእስላማዊ መንግስት ጥንስስነት በመክሰስ ከሩሲያ ህዝብ ድጋፍ ለማግኘትም ሆነ ከአለም ማህበረሰብ ለማግለል ያደረገዉን ሙከራ አሰናከለበት፡፡ በተለይም የቼችንያ መሪዎች የጉዞ መስመር ሴኩላርና ዲሞክራሳዊ መሆን የሩሲያ ህዝቦች የአገራቸው መንግስት በቼችንያ ላይ የሚያደርሰዉን ጥቃት እንዲያቆም ከፍተኛ ግፊት እንዲያደርሱበት ከማድረጉም በላይ የሩሲያ ሰራዊት የመዋጋት ፊላጎቱን እንዲያጣና ግዙፉ የሩሲያ ጦር በቼችንያ ለተደጋጋሚ አዋራጅ ሽንፈቶች ተዳረገ፡፡ ከአለም አቀፍ ማህበረሰብም የሚደርስበት ጫና ከእለት ወደ እለት እየጨመረ ሄደ፡፡

በቀድሞዋ የሶቭት ህብረት የደህንነት ፣ የጦር ሰራዊት እና የአስተዳደር መዋቅሮች ዉስጥ የመስራት አጋጣሚ አግኝተው የነበሩ የአዲሲቱ ቼቼኒያ ሴኩላር መሪዎች የሩሲያን የስለላ ድርጅት የረቀቀ ደባ አስቀድመው ያዉቁ ስለነበር ምንም እንኳን አገራቸው በሩሲያ ተደጋጋሚ ጥቃትና ትንኮሳ ቢደርስባትም ሴኩላርና ዲሞክራሳዊ የሆነው ጎዳና ፈተናው አናሳ መሆኑን ተገንዝበው ይህን መስመር አጥብቀው ለመከተል ወሰኑ፡፡ ይህ አካሄዳቸው የሩሲያ መንግስት የቼችኒያን መንግስት ለሩሲያ የደህንነት አደጋ አስመስሎ በማቅረብ ከሩሲያ ህዝብና ሰራዊት ድጋፍ ለማግኘትም ሆነ ከአለም አቀፍ ማህበረሰብ ለመነጠል የምያደርገዉን ጥረት አከሸፈበት፡፡ ስለዝህ የቼችኒያን ሴኩላር መሪዎች ለማንበርከክ ፕሮፖጋንዳ የመንዛት ስራ ብቻዉን በቂ እንዳልሆነ ግልጽ ሆነ፡፡ አላማዉን ከግብ ለማድረስ ቆርጦ የተነሳው የሩሲያ መንግስት የወታደራዊና ሲቪል የመረጃና ደህንነት ተቋማቱን (Federal Security Service (FSB), Russia’s domestic intelligence agency) ሚና በማጠናከር፡-

- ሴኩላርና ዲሞክራሳዊ በሆነው መርሆ ጸንተው የገፉትን መሪዎች ነጥሎ በማውጣት ቀዳሚ የግድያ ኢላማዎች በማድረግ የቼቼንያን የአመራር አካል ሰኩላርና ዲሞክራሳዊ የሆነውን ጎዳና ከምከተሉ መሪዎች ተጽእኖ የማላቀቅ ስራ መስራት (በዚህም እቅዳቸው መሰረት ዱዳየቭን በ 1996 ዓል እና አስላን ማስካሃዶቭን ደግሞ በ 2005 ዓ ል ገደሉ)

- ከተደጋጋሚ ጥቃትና ትንኮሳዎች በስተጀርባ የተሸሸገዉን ሴራ አስከፊነት አስቀድመው ስለተረዱ መስዋእትነት እየከፈሉ ሴኩላርራዊና ዲሞክራሳዊ የሆነውን ጎዳና የሙጥኝ ብለው በመያዛቸው ምክንያት መሰናክል የሆኑበትን የቼቼንያን የፖለቲካ ልሂቃን እስልምናን የከዱ ፣ አለማዊያን አድርጎ የሚከሱ የእምነት አባቶች ተደማጭነት እንዲያገኙ በማገዝ (ከእምነት አባቶቹ በተሰወረ መልክ) ሴኩላር እይታ ያላቸዉን እንዲያዳክሙ መስራት

- በሩሲያ ተደጋጋሚ ጥቃት የቅርብ ዘመዶቻቸዉ በግፍ ስለተገደሉባቸዉ በቁጣ የገነፍሉና ለበቀል ለመነሳሳት ፍንጭ ያሳዩ ተጽእኖ ፈጣሪ ግለሰቦችንና ተከታዮቻቸዉን ለጂሃድ እንድበረታቱ በቡድኖች ውስጥ ያሰማራቸውን ሰርጎገብ ወኪሎቻቸውን በመጠቀም ወደ ጫፍ መግፋት

- የሴኩላራዊ ፖለቲካ መንገድ የመረጡ ቡድኖች ከ 1991 እስከ 1997 የተጓዙበት መንገድ መስዋእትነት እያስከፈለ የነበረ ጎዳና ቢሆንም የተሻለ አማራጭ ስለመሆኑ መሞገት የተያያዙትን አካላት በፈጣሪያቸው የማይመኩ አድርገው የሚኮንኑ የእምነት አባቶችና ተጽእኖ ፈጣሪ ግለሰቦች ጎልተው እንዲወጡ ከበስተጀርባ በመስራት ሰኩላር ሃይሉን ማዳከም

- ለስልጣን ሲሉ ህዝባቸውን የከዱ ግለሰቦችን በጥቅም በመደለል ወደ ጽንፍ የወጣ እይታ ያላቸዉን በፖለቲካ ዉስጥ ይሳተፉ የነበሩ በቸችኒያ ተጽእኖ ፈጣሪ የነበሩ ግለሰቦችን ሰኩላር በሆነው የቸችኒያ መንግስት ላይ እንዲያነሳሱና ሴኩላር ሃይሎች እንዲፍረከረኩ መስራት

በተጓዳኝ የሩሲያ የሰለላ ድርጅቶች በጋለ ስሜት እምነታቸውን ለማገልገል ፍላጎት የነበራቸውን ነገር ግን ስለእምነታቸውም ሆነ ስለፖለቲካ በቂ ግንዛቤ ያልነበራቸዉን ግለሰቦች ጀግኖቹ ሙጃሂድኖች በሚል መጠሪያ በማበረታታት ብቸኛው አዋጭ መንገድ ጂሃድ ነው የሚል ሃሳብ የሚያራምዱ ግለሰቦችም ሆኑ ስብስቦች ተጠናክረው የኮካሰስ ኢሜሬት በምል ስያሜ የሚጠራ በሰሜን ኮካሰስ (Chechenia, Destan, Ossetia) እስላማዊ መንግስት ለመመስረት አላማ ያለውን ድርጅት መፍጠራቸውን ይፋ አንድያደርጉ የሩሲያ የሰለላ ድርጅቶች በእጅ አዙር ትልቅ ሚና ተጫወተ።

ሰኩላር የነበረዉን መስመር አዋጭነት ከጅምሩ ያልተቀበሉትን ፣ ቀጣይነት የነበረው የሩሲያ ጥቃት ባስከፈለው ከፍተኛ መስዋእትነት ምክኒያት ከግዜ ኋላ በሰኩላር የትግል ጉዞ ላይእምነት እያጡ የመጡ ግለሰቦችንና ስብስቦችን ጂሃድ እንድያዉጁ በመጎትጎት ያሳወጁ በስብስቦች ውስጥ ሰርገው የገቡ የሩሲያ የስለላ ደርጅት ቅጥረኞች የሩሲያ መንግስት በሰኩላር ሃይሎች ላይ የማያዳግም ጥቃት በመፈጸም በቺቺንያ ፖለቲካ ዉስጥ የያዙትን ጉልህ ስፍራ እንድያሳጣቸው ከፈለጉ ሩሲያ ላይ ትንኮሳ መፈጸም እንዳለባቸው ያነሳሱ ጀመር።

ለዚህ ሴራ ከተጋለጡት ተጽእኖ ፈጣሪ ግለሰቦች አንዱ ሰኩላር በነበረው በአስላን መንግስት ዉስጥ የምክትል ጠ/ምንስተርነት ስፍራ የነበረው ሻሚል ባሳየቭ እንደሆነ ይነገራል ። ባሳየቭ በ1998 ፕረዝደንት አስላን በሩሲያ ላይ የተለሳለሰ አቋም ስላለው መወገድ አለበት የሚል ክስ አቅርቦ ዉድቅ ሲለሆነበት በ1999 በሰሜን ኮካሰስ እስላማዊ መንግስት ለመመስረት አላማ አለኝ የሚለውን ድርጅት ተቀላቀለ ። ይህም ክስተት በሰኩላርነቱ ይታወቅ የነበረዉን የቺቺያን እንቅስቃሰ ይበልጥ እንዲዳከም ከማድረጉም በላይ በቂ ዝግጅት ሳያደርግ ጂሃድ ያወጀው ቡድን ጎልቶ እንዲወጣ በማስቻሉ ሰኩላር የነበረው ፍልምያ ወደ ጂሃድ ጦርነት እንድሸጋገር ሁኔታዎችን አመቻቸ።

የሩሲያ የስለላ ደርጅት ያሰማራቸው ሰርጎ ገቦች ጉትጎታ ወጥመድ ውስጥ በመውደቃቸው በሃምሌ ወር 1999 የባሳየቭ ሃይሎች የቸችኒያ አጎራባች በሆነችው ደግስታን ግዛት ጥቃት አደረሱ ። መሰል ትንኮሳዎችን ይጠባበቅ የነበረው የሩሲያ መንግስት ባሳየቭና መሰሎቹ ይጠብቁት እንደ ነበረው ውንጀላው በስኩላር ሃይሎች ላይ ብቻ ያነጣጠረ ሳይሆን ጂሃድ ባወጁትም ላይ ነበር።

በደግስታን ግዛት ላይ የተደረገዉን ጥቃት ተከትሎ የሩሲያ መንስት ግዜ ሳይፈጅ የኮካሰስ ኢሜሬት ብሎ ራሱን የሰየመው ድርጅት ፥

- በቸችንያ የነበረዉን ችግር ወደ ተቀሩት የሰሜን ኮካሰስ ግዛቶች ለማዛመት የተነሳ በሩሲያ አንድነትና ደህንነት ላይ ከፍተኛ አደጋ የጋረጠ የጠላት ቅጥረኛ ነው
- በ 1980ዎቹ ለምእራብ አገሮች መሳሪያ በመሆን በአፍጋንስታን የዘመተዉን የሶቭት ሃይል በመዋጋት የሶቭት ህብረት ተበትኖ ሩሲያ እንድትዋረድና እንድትዳከም የረዱ ሙጃሂዲኖች አሁን ስማቸዉን ወደ የኮካሰስ ኢሜሬት በመቀየር ሩሲያን ለመበተን በድፍረት ከደጅህ ቆመዋል የሚል ፕሮፖጋንዳ በመንዛት በአጭር ግዜ ውስጥ ከዜጎቹ ከፍተኛ ድጋፍ ለማግኘት ከመቻሉ ባሻገር በቸችንያ ላይ በመቀጠል ለፈጸመው ጭፍጨፋ ከምእራቡ አለም ወቀሳ እንዳይቀርብበት ለማድረግ ችሏል ።

የሩሲያ የሰለላ ድርጅቶች በረቀቀ ሴራቸዉ ስለ አዋጭ የትግል ጎዳና የተለየ እይታ የነበራቸውን የቸችንያ ዜጎች በመጠቀም ከዘጠኝ አመታት በላይ የሩሲያን ሃይል ለመመከት ችሎ የነበረውን የሰኩላር ጎራ ካዳከሙ በኋላ በግላጭ ያገኙትን ጂሃድ ያወጀውን ሃይል ከህዝባቸው ባገኙት ከፍተኛ ድጋፍና አለም አቀፍ ማህበረሰብ ያሳየዉን ስምምነት በመጠቀም በቸችንያ ህዝብ ላይ እጅግ ዘግናኝ የሆነ ከልካይ ያልታየበትን ጭፍጨፋ ፈጸሙ።

በቼቺኒያ ተቀስቅሶ የነበረው ፍልምያ ሴኩላር ገፅታውን በማጣት ወደ ጂሃዳዊ እንቅስቃሴ እንዲለወጥ ካደረገ ቡሃላ የሩስያ መንግስት በሃገር ውስጥ ያለውን ድጋፍ በማጠናከር ከውጭ የሚደረግበትን ጫና በተለይም ከምእራቡ ዓለም ይሰነዘርበት የነበረውን ወቀሳ እና ግፊት በማቀዛቀዝ በቼችንያ ሃይሎች ላይ ከፍተኛ መጠን ያለው ጉዳት ለማድረስ ሃይሉን አሰማራ ፡፡ በዚህም ሁኔታ ለዘጠኝ አመታት የሩስያን ሃይል ሲገዳደር የቆየው ሰኩላር የቼቼንያ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ከውስጥ የተሳሳተ የትግል ጉዞ በመረጡ ቡድኖች ስለተሸረሸረ የሩሲያን ሃይል ለመመከት የነበረው ብቃት ከፉኛ ተዳከመ ፡፡

የሩሲያ መንግስት የተዳከመውን የቼቺኒያ ህዝብ እንቅስቃሴ ሙሉ ለሙሉ ለመቆጣጠር እና ለማዳፈን ባደረሰው ብርቱ ጥቃት በቼቺኒያ የሚደረገው እንቅስቃሴ ከተቀናጀ ዉጊያ ወደ ተበታተነ እና የማይናበብ የደፈጣ ውግያ እንዲገባ አስገደደው፡፡ የተዳከመዉም ትግል በየፊናቸው የምጓዙ የተለያዩ ትንንሽ የጦር አበጋዞች ( war loards) ወደ ሚመሩት እንቅስቃሴ ያመራ ጀመር ፡፡

እንቅስቃሴውም ከደረሰበት ውድቀት ለረዥም አመታት ሳያገግም በመቅረቱ የቼቺኒያ ተዋጊዎች ለበርካታ አመታት በሩስያ ውስጥ በሲቪል ላይ ጥቃትን የሚፈፅሙ የሽብርተኛ ድርጅቶች ሆነው እንዲያሽቆለቁሉ አድርጓቸዋል፡፡ ለዚህም በምሳሌነት የሚጠቀሰው ከሁለት መቶ ሰዎች በላይ ህይወት መጥፋት ምክንያት የሆነው በሞስኮ ቲያትር ቤት የተፈፀመው እገታና የጥቃት እርምጃቸው ነበር ፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ በመካከለኛው ምስራቅ እራሱን እስላማዊ መንግስት ብሎ የጠራው የሽብር ቡድን በመነሳቱ ይህንን አጋጣሚ ለመጠቀም የፈለገው የሩስያ የስለላ ድርጅት ሌላ ሴራ መሸረብ ጀመረ ፡፡ የእቅዱ የመጀመሪያ ክፍል በ 2011 በቼቺንያ በጂሃድ ፍልምያ ተሰማርተዉ የነበሩም ሆኑ ቀድሞ የጂሃድ ታጋዮች የነበሩ ነገር ግን ወደ ሰላማዊ ኑሮ የተመለሱ የቸችንያ ተወላጆች የሩስያን ድንበር ለቀው ወደ ሶርያ ሆነ ኢራቅ በመሄድ ሙስሊም ወንድሞቻቸውን በጂሃድ ለማገዝ ከፈለጉ የሩሲያ መንግስት ለጉዞ አስፈለጊ የሆኑትን (ፓስፖርት፣ ትኬት፣ ገንዘብ ወዘተ ) በማቅረብ ለመተባበር ዝግጁ መሆኑን በደህንነት ድርጅቶቶቹ በተመለመሉ አደራዳሪዎች ብለው በሚጠሯቸው ግለሰቦች በማግባባት ወደ መካከለኛው ምስራቅ መሸኘት ነበር፡፡ የዚህ ሴራ ዋና ግቦች፥

- ልምድ ያላቸውን የጅሃድ ተዋጊዎች ከቼቺኒያ ምድር ወደ ሁለቱ አገሮች እንዲፈልሱ በማድረግ ከቼቺንያና ከሩሲያ በማራቅ አልፎ አልፎ የምደረጉ የደፈጣና የአጥፍቶ መጥፋት ጥቃቶችን መቀነስ ብሎም ማስቀረት፡፡

- የዉግያ ልምድ ያላቸዉንና ለመስዋእትነት ዝግጁ የሆኑ የጂሃድ ተጋዳዮችን በሶሪያና በኢራቅ በማሰማራት በዝያ የምገኙትን ከአሜሪካንና ከምእራብ አገሮች የሄዱትን ሃይሎች እንድዋጉ በማድረግ በ1980ዎቹ የምእራቡ አለም በአፍጋኒስታን ያደረሰበትን ኪሳራ መበቀል

- በአለም ዙሪያ በየአገራቸው በተበተኑ ግዜ ነጥሎ ለማውጣትም ሆነ ለመዋጋት አዳጋች የሆኑትን ከተለያዩ አገሮች ወደ ሶሪያና ኢራቅ ፈልሰው በጂሃድ ተሰማርተናል የሚሉትን በዉስን ክልል ዉስጥ እንድሰባሰቡ በማድረግ ከሌሎች አገሮች ጋር ሃይልን በማጣመር መፈናፈኛ አሳጥቶ ከክልሉ ሳይወጡ መፍጀት ወይንም መማረክ

- እነዚሁኑ ከአገሩ አግባብቶ ወደ መካከለኛው ምስራቅ የላካቸውን መሰል ተዋጊዎችን ከአለም አቀፍ ማህበረሰብ ጎን ሆኖ በመዋጋት አሸባሪነትን ለመፋለም ከቆረጡ አገሮች ተራ ራሱን በማሰለፍ ገጽታዉን ማደስ

የሩስያ የስለላ ድርጅት ይህን በማድረጉ በአቅራብያው ካለው የቼቺኒያ ግዛት የሽምቅ ተዋጊዎችን ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ እንዲያሽቆለቁልችችና አልፈው አልፈው ያደርሱት የነበረውንም ጥቃት ከግማሽ በላይ ለመቀነስ እንደቻለ ዘግቧል፡፡

እነዚህ ሃይሎች የምእራቡን ሃይል እንዲፈታተኑ በማድረግ በአፍጋኒስታን ደርሶበት የነበረውን የሽንፈት ቂም በምእራቡ አለምም ላይ እንዲደርስ ለማድረግ እየተገለገለባቸው ቢሆንም የምእራቡ አለም በአፍጋንስታን ካደረሰበት ጉዳት ጋር ሲነጻጸር የጎላ አይደለም ፡፡

ከዛም በተጨማሪ ከምእራቡ ዓለም ጋር የፀረ-ሽብር ግብረ-ሃይል በመፍጠር የፀረ-ሽብር ሻምፒዮን ሆኖ በዓለም አቀፍም መድረክ ጎልቶ ለመውጣት ያለመው ግብ እንደተሳካለት ባለሙያዎች ይናገራሉ።

እንግዲህ በዚህ መልኩ ሩስያ የፈጠረቻቸውን የፅንፈኛ ቡድኖች በቼቺንያ የሴኩላር እንቅስቃሴን ለማዳከም ከተገለገለችባቸው በኃላ ISIS እውቅና ካገኘበት ግዜ ጀምሮ ደግሞ ለሌላ ተልእኮ ማስፈጸምያነት እየተገለገለባቸው በመሆኑ ዛሬም ቢሆን ሳያውቁት የሩስያን የስለላ ድርጅት ተልኮ በማስፈፀም ላይ ይገኛሉ።

አዋጭ ያልሆነ መንገድ የተከተለው የትግል ሂደት ጣጣው በዚህ አላበቃም። የሩስያ የፀጥታ ሃላፊዎች አብዛኛዎቹ ተዋጊዎች ከነበሩበት የሚስጥር ስፍራ ወደ ሶርያ እና ኢራቅ እንዲፈልሱ ካደረጉ ቡኃላ በከተማ ውስጥ ያሉትን ወጣቶች በተለይም ለወደፊት ለሙብት ሊፋለሙ ይችሉ ይሆናል ብለው የሚጠረጥሯቸውን ከአማፅያን ቡድኖች እና ሽብርተኞች ጋር ግንኙነት አላችሁ በማለት እየወነጀሉ ጥቁር መዝገብ ውስጥ በማስገባት በየግዜው ማንገላታት እና ማሸማቀቅን እንደ አንድ እቅድ በመያዝ ሰላማዊ ህይዎት የሚችገፉ ወጣቶች በወከባ ብዛት ተሰላችተው ሃገራቸውን ለቀው ወደ ኢራቅ እና ሶርያ እንዲያቀኑ ሌላ በር ከፍተዋል። በዚህ መስክ ውጤት ያገኙበት ሌላው ሴራ የአካባቢ ሚሊሺያዎች ወጣቶችን በማዋከብ እና እረፍት በመንሳት የውግያ ዝንባለ የሌችችላቸዉንና ወደ መካከለኛው ምስራቅ ለመኮብለል ፍላጎት ያላሳዩትን ለብርቱ አይነት የማህበራዊ እና ስነ ልቦናዊ ጫና እንድጋለጡ በማድረግ የመዋረድ ስሜት ተሰምቷቸው ከቼቺንያ ግዛት እንዲለቁ እና እንዲበታተኑ አድርገዋል። ለደፈጣ ተዋጊዎች ብቻ ሳይሆን ገና ለወደፊት ነቅቶ ሙብቱን ሊጠይቅ ይችላል ከሚል ህሳቤ እና መላምት በመነሳት በማህበረሰቡ ውስጥ ለውጥ ሊያመጡ ይችላሉ ተብሎ የሚታሰቡትን ወጣቶች በሙሉ ከግዛቲቷ እንዲለቁ ዛሬም ድረስ ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ።

እንግዲህ በዚህ መልክ የፈጠሩትን የጂሃድ ቡድን ለዚህ ሶስተኛ አገልግሎት በመጠቀም በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ ሳይሆን ሶስት ወፍ የመጣልን የተንኮል ጥበብ በስራ ላይ ማዋላቸዉን ከዝህች አጭር ጽሁፍ ለመገንዘብ የቻልን ግለሰቦች ምን አይነት ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅብናል? እነዚህን እውነታዎች በማስተንተን የአምባገነኖችን ሴራ ዉስብስብነትና ጥልቀት ተረድተን ከዚህ አይነት ደባ ለመጠበቅ የየበኩላችንን ጥረት በማድረግ ራሳችንን፣ ማህበረሰባችንና አገራችንን ከጥፋት ለመከላከል ተግቶ መስራት የሁላችንም ድርሻ ነው ። አላህ ይርዳን።

ከመካ ጉማ

12 May 2017